በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 215534

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች**፡- አቶ ዉድነህ መንገሻ፡- ቀርበዋል

**ተጠሪዎች**፡- 1. የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት አካባቢ ደን እና አየር ንብረት ለዉጥ ቁጥጥር ባለስልጣን፡- ተወካይ አቶ ደመላሽ ቀረቡ

2. የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ፐብሊክና የሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ፡- ወ/ሮ ጥሩወርቅ እንደሻው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ

ተሰጥቷል

## ፍርድ

ጉዳዩ የመንግስት ሠራተኛ የደረጃ ዕድገት አሰጣጥን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልላዊ መንግስት ስቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ በ1ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት የአካባቢ ጥበቃ አየር ንብረት ለዉጥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የስራ መደብ ላይ ተወዳድረዉ ምደባ ከተሰጣቸዉ በኋላ የ2ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት እንስፔክሽን ጉዳዩን ያለስልጣኑ አይቶ የተሰጣቸዉን ምደባ ሰርዞ ለሌላ ግለሰብ የሰጠ መሆኑን ጠቅሰዉ የእንስፔክሽኑ ዉሳኔ እንዲሻርላቸዉ የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪዎች ለአቤቱታዉ በሰጡት መልስ 1ኛ ተጠሪ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ደግፎ የተከራከረ ሲሆን፣ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ መደቡ በጂኢጄ መሠረት ለቀጥተኛ የስራ ልምድ 100% ዋጋ የሚሰጥ ሲሆን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በዉድድሩም አመልካች የነበራቸዉ ቀጥተኛ የስራ ልምድ 9 ዓመት ከ1 ወር ከ17 ቀን ሲሆን ከአመልካች ጋር የተወዳደሩት ሌላ ግለሰብ ከ10 ዓመት በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያላቸዉ መሆኑ በመረጋገጡ የ2ኛ ተጠሪ እንስፔክሽን ክፍል በህግ በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት የአመልካችን ምደባ በመሰረዝ የሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተዉ የክልሉ ስቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በጂኢጂ መመሪያ መሠረት ለመደቡ የሚፈለገዉ የስራ ልምድ ቀጥተኛ እንጂ ተቀራራቢ አለመሆኑን፣ በዚህ ረገድ የአመልካች ቀጥተኛ የስራ ልምድ 9 ዓመት ከ 1 ወር ሲሆን ከአመልካች ጋር የተወዳደሩት ግለሰብ ቀጥተኛ የስራ ልምድ 11 ዓመት ከ 7ወር ያላቸዉ ስለመሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ የተጠሪ ቢሮ እንስፔክሽን የሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ ችሎትም የአስተዳደር ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔም ባለመስማማት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን፣ ሰበር ሰሚዉ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን አስቀርቦ የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2014 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ የሰበር አቤቱታ የ2ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት እንስፔክሽን የክልሉ የመንግስት ሠራተኞች ህግጋትን በትክክል ስራ ላይ መዋል አለመዋላቸዉን የኦዲት ስራ በመስራት አካሄዶችን የማረም እንጂ ምደባን አስመልክቶ የሚነሱ ቅሬታዎችን መርምሮ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን የለዉም፡፡ የከተሞች አደረጃጀት ፕላን ዝግጅት ክትትል ስራ ሂደት አስተባባሪ ሆኜ የሰራሁት የ8 ዓመት የስራ ልምድ ወደ ጎን በመተዉ ፍርድ ቤቱ የተሻረ ህግ በመጠቀም መመሪያ ቁጥር 15/2009 ጂኢጂ መሠረት በማድረግ የስራ ልምድ 100% ግንኙነት ሊኖረዉ ይገባል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን ጠቅሰዉ ታርሞ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በዚህም መሠረት 2ኛ ተጠሪ መጋቢት 07 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የአመልካች የስራ ልምድ ለስራ መደቡ ያለዉ አግባብነት በመመሪያ ቁጥር 20/2011 አንቀጽ 62(3) መሰረት ታይቶ የተሰጠ እንጂ አመልካች እንደሚሉት በመመሪያ ቁጥር 15/2009 መሠረት አለመሆኑን እና ከዚህም አንፃር ሲታይ አመልካች ያላቸዉ ቀጥተኛ የስራ ልምድ 9 ዓመት ከ1 ወር ሲሆን አቶ ተፈራ ማተቤ የተባሉት ሌላኛዉ ተወዳዳሪ ግን 11 ዓመት ከ7 ወር ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያላቸዉ መሆኑ መረጋገጡን፤ 2ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት በማናቸዉም መንገድ ህግ መጣሱን ወይም አድሎ መፈጸሙን ከደረሰበት ትክክል ያልሆነዉን አሠራር የማስተካከል በአዋጅ ቁጥር 175/2011 አንቀጽ 95 መሠረት ስልጣን የተሰጠዉ በመሆኑ አድሎ ተፈጽሞብኛል በማለት በአንድ ሠራተኛ የቀረበዉን ጥቆማ መነሻ በማድረግ እንስፔክሽኑ መርምሮ ዉሳኔ መስጠቱ ከስልጣኑ ዉጪ ነዉ ለማለት የሚያስችል የህግ መሠረት የለም በማለት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተከራክሯል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ስራ መደቡን መስጠቱን ጠቅሶ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የ2ኛ ተጠሪን መልስ አስመልክቶ ባቀረበዉ የመልስ መልስ ክርክሩን በማጠናከር ተከራረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም በክልሉ ሲቭል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የጸናዉን ዉሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ በደ/ብ/ብ/ክልል ስቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ዉድቅ በማድረግ ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ አመልካች የብዙ ዓመት የስራ ልምድ ያላቸዉ ቢሆንም ለክርክሩ መነሻ ለሆነዉ የስራ መደብ በቀጥታ ተያያዥነት ያለዉ 9 ዓመት ከ 1ወር ብቻ መሆኑን እና በአንፃሩ ከአመልካች ጋር የተወዳደሩት ግለሰብ ከ11 ዓመት በላይ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያላቸዉ መሆኑን፣ በጀኢጀ መመሪያ መሠረት ተቀባይነት ያለዉ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ብቻ መሆኑ መረጋገጡን በመጥቀስ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተዉ የደ/ብ/ብ/ህዝቦች መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የሲቭል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ በዚህ ረገድ የደረሰበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ በመቀበል እንዲሁም የክልሉ ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት አመልካች የክልሉ የመንገግስት ሠራተኞች ምልመላና መረጣ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 20/11 አንቀጽ 25(4) ላይ በተመለከተዉ መስፈርት መሠረት ለመደቡ ቀጥተኛ የስራ ልምድ ያላቸዉ ሌላኛዉ ተወዳዳሪ አቶ ተፈራ ማተቤ ሲሆኑ አመልካች ይህን መስፈርት የማያሟሉ መሆኑን አለመሆናቸዉ መረጋገጡን እና የ2ኛ ተጠሪ ቢሮም ህግና መመሪያን በመጣስ የተከናወኑ ተግባራትን የማረም ስልጣን ያለዉ መሆኑን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ ያጸና ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ስለመሆኑ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚል ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ የሚሰጠዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የክልሉ ስቪል ሰርቪስ ፍርድ ቤት እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን ክርክር ዉድቅ በማድረግ የሰጡትን ዉሳኔ በማጽናት፣ የሰጠዉ ዉሳኔ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 77404 ላይ መስከረም 07 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*